# የጀዋር መሃመድ የተሳሳቱ ፖለቲካዊ እይታዎች

ትግራይ ኦንላይን, Sept. 03, 2013

(በአዲሱ አረጋ ቂጤሳ)

ወጣቱ የፖለቲካ ተንታኝ እና የኦሮሞ ብሄርተኛ ጀዋር መሃመድ ሰሞኑን ስለ ኦሮሞ ህዝብና የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፣ ከኢቲዮ ቲዩብ ድረ ገጽ ጋር ቃለ ምልልስ አድርጎ ነበር፡፡ በቃለ ምልልሱ ያራመዳቸዉ የፖለቲካ አስተሳሰቦችም አነጋጋሪ ሆነዉ ሰንብተዋል፡፡ እኔም በራሴ አተያይ ጀዋር ካራመዳቸዉ የፖለቲካ አስተሳሰቦች የተሳሳቱ ናቸዉ ብ§ በማስባቸዉ ላይ ሀሳቤን አቀርባለሁ፡፡ ጀዋር በቃለ ምልልሱ የኦሮሞ ህዝብ በአሁኑ ወቅት የኢኮኖሚ፣ የማንነት እና ሌሎች ፖለቲካዊ ጭቆናዎች እየደረሱበት ነዉ፤ ሌሎች ኢትዮጲያዉያን ለኦሮሞ ህዝብ ስር ሰደደ ጥላቻ እና ፍራቻ (በርሱ አገላለጽ #ኦሮሞፎቢያ;) አለባቸዉ በማለት ይከራከራል፡፡ ለዚህ ፖለቲካዊ ችግር መፍትሄዉ አሁን ያለዉን ስርዓት በትጥቅ ትግል በመደርመስ «የኦሮሚያ ሪፓብሊክ» ማቋቋም ነዉ ብሎ ያምናል፡፡

## 1. የኦሮሞ ህዝብ «የኢኮኖሚ ጭቆና»

በኦሮሞ ህዝብ የትግል ታሪክ ፍትሃዊ ኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ጥያቄ አንዱ እና ዋነኛዉ ጥያቄ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ከፊዉዳሉ ስርዐት ጀምሮ እስከ ደርግ ዉድቀት ድረስ ኦሮሞ ህዝብ እንደ ሌሎች ኢትዮጲያዉያን በገጠር የመሬት ባለቤት እና በጉልበቱ በላቡ ባመረተዉ ምርት ተጠቃሚ እንዳልነበረ ሁላችንም የምናዉቀዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ ነጋዴዉም ቢሆን ሃብት የማፍራት መብቱ ከአምስት መቶ ሺኅ ብር ማለፍ እንደማይችል የታወቀ ጉዳይ ነዉ፡፡ በርግጥ እስከ ደርግ ዉድቀት ድረስ ኦሮሞ ህዝብ ኢኮኖሚ ጭቆናዉ ገፈት ቀማሽ ነበር፡፡ በወቅቱ ነበረዉን ጭቆናም አንድም ቀን አሜን ብሎ ተቀብሎ አያዉቅም፡፡ እንደሌሎቹ የኢትዮጲያ ህዝቦች ሁሉ ታግሏል፡፡ መስዋዕትነት ከፍሎም ጨቋኝ ስርአቶችን ገርስሷል፡፡ ከኦሮሞ ህዝብ መሰረታዊ ኢኮኖሚ ጥያቄዎች ዉስጥ ዋነኛዉ የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ እና በላቡ ባመረተዉ ምርት በነጻነት የመጠቀም ጥያቄ ነበር፡፡ እንደእኔ አመለካከት አሁን ባለዉ ተጨባጭ ሁኔታ እነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ አግኝተዋል፡፡ ህገ መንግስታዊ ዋስትና አግኝተዋል፡፡ በገጠር ያለዉ የኦሮሞ አርሶ አደር የመሬት ባለቤትነቱ ተረጋግጧል፡፡ አርሶ አደሩ ባለዉ መሬት ላይ የልፋቱና የላቡ ዋጋ የሆነዉን ምርቱን በፈለገዉ ጊዜ፣በፈለገዉ ቦታ፣ በፈለገዉ ዋጋ የመሸጥ እና ምርቱን እንደልቡ የመጠቀም መብት ተጎናጽፏል፡፡ ይልቁንም ምርት እና ምርታማነቱን በማሳደግ ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ አኗኗር ዜይቤ ተላቆ ለገበያ እንዲያመርት ሰፋ ያለ የግብርና ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት እና ድጋፎችን በማግኘት ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህም የተነሳ ከእጅ ወደአፍ ነበረዉ ኦሮሞ አርሶ አደሮች ኑሮ እንደሌሎቹ ኢትዮጲዉያን ወንድሞቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመሻሻል ላይ ይገኛል፡፡ እንደቀደሙት ስርዓቶች ኦሮሞ አርሶ አደሮች በፊዉዳላዊዉ የመሬት ስሪት ጭሰኞች አይደሉም፡፡ የመሬት ባለቤት ናቸዉ፡፡ በደርግ ሶሻሊስታዊ ስርዓት ጊዜ እንደነበረዉ በኮታ እና በሌሎች አሰራሮች ምርቱን እንደፈለገዉ የመጠቀም ገደብ የለም፡፡ በከተሞችም ስራ አጥነትን ለማስወገድ በሚደረገዉ ትግል ኦሮሞ ወጣቶች እና ሴቶች በጥቃቅን አና አነስተኛ ተቋማት ግንባር ቀደም ተሳታፊዎችና ተጠቃሚዎች ናቸዉ፡፡ ወደ ባለሃብትነት የተሸጋገሩም በርካታ ናቸዉ፡፡ በንግድ እና በሌሎች የሙያ መስኮች የተሰማሩ የብሄሩ ተወላጆች አንደማንኛዉም ኢትዮጲያዊ ምንም አድልኦ እና ልዩነት ሳይደረግባቸዉ በልፋታቸዉ ልክ ሰርተዉ በመጠቀም በነጻነት በመኖር ላይ ይገኛሉ፡፡ በሃገሪቱ እየተስፋፋ ካለዉ መሰረተ ልማት ዝርጋታ የኦሮሞ ህዝብ ግንባር ቀደም ተጠቃሚ መሆኑ ያፈጠጠ ሃቅ ነዉ፡፡ ታዲያ ጀዋር የሚለዉ የኢኮኖሚ ጭቆና ከወደየት የመጣ ነዉ? በእኔ እምነት እነጀዋር «የኦሮሞ ህዝብ ሆይ የኢኮኖሚ ጭቆና አለብህ ፡፡ ከዚህ የኢኮኖሚ ጭቆና ልናላቅቅህ ነዉ የምንታገለዉ፡፡ ለዚህም መፍትሄዉ መገንጠል ነዉና ተነስ!» ብለዉ አጀንዳ ይዘዉ ወደ ህዘቡ ቢወርዱ አሁን ባለዉ ተጨባጭ ሁኔታ ገበሬዉ በሜንጫ ማጅራታቸዉን ብሎ እንደሚያባርራቸዉ አልጠራጠርም፡፡እነጀዋር ሌላ የማታገያ አጀንዳ ይፈልጉ እንጂ የህዝቡ ኢኮኖሚ ጥያቄ ምላሽ አግኝቷል፡ በርግጥ ድህነቱ ሙሉ በሙሉ ተወግዷል ማለት አይቻልም፡፡ ድህነቱ እንዲቀጠል የሚፈልግ የኢኮኖሚ ጭቆናን የሚያራምድ የድህነት ዘበኛ የሆነ ሥርኣት ግን የለም፡፡

## 2. «የፖለቲካ ጭቆናና» «ኦሮሞፎቢያ»

ጀዋር ያራመደዉ ሌላዉ የተሳሳተ አስተሳሰብ ህዝቡ በአሁኑ ፌዴራላዊ ስርዐት ፖለቲካዊ መብቶቹ ያልተከበሩለት፤ በ ሌሎች ኢትጲያዉያን ዘንድ ስር ሰደደ ሁኔታ የሚጠላ እና በጥርጣሬ አይን የሚታይ ህዝብ ስለሆነ «የኦሮሚያን ሪፓብሊክ» መመስረት ብቸኛዉ መፍትሄ ብሎ መደምደሙ ነዉ፡፡

### 2.1 «የፖለቲካ ጭቆና»

እንደሚታወቀዉ የኦሮሞ ህዝብ ባደረገዉ እልህ አስጨራሽ ትግልና በከፈለዉ መስዋዕትነት የህዝቡ ላይ ተጭኖ ነበረዉ ብሄራዊ ጭቆና ላይመለስ ተንኮታኩቷል፡፡ የህዝቡ ብሄራዊ የማንነት ጥያቄ ህገ መንግስታዊ ዋስትናን አግኝቶ ህዝቡ ራስን በራስ የማስተዳደር፣ በራሱ ቋንቋ የመማር (እስከ ማስተርስ ድግሪ ድረስ)፣ በራሱ ቋንቋ የመዳኘት ፣ሃሳቡን በነጻነት የመግለጽ ፣ የመደራጀት ወዘተ መብቶቹ ህገመንግስታዊ ዋስትና አግኝተዉ በፌዴራላዊ ስርአቱ ዉስጥ ከሌሎች ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ጋር በመሆን በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ኢትዮጲያዊነቱን ተቀብሎ ፖለቲካዊ መብቱ ተከብሮለት እየኖረ ይገኛል፡፡ በአዲሲቷ ኢትዮጲያ ዉስጥም የኦሮሞ ህዝብ የኢትጵያ አንድነት የጀርባ አጥንት እና ግንድ እንደሆነ አረጋግጧል፡፡ ግንድ ደግሞ አይገነጠልም፡፡ ህዝቡ በአዲሲቷ ኢትዮጲያ እንደህዝብ እዉቅና ያለዉ፣ የራሱን ክልላዊ መንግስት መስርቶ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድር፣ ባህሉን እምነቱን እና የማንነት እሴቶቹን ያለምንም ገደብ በማሳደግ ላይ የሚገኝ፣ ሰብዓዊ እና ዴመክራሲያዊ መብቶቹ የተረጋገጡለት ህዝብ ነዉ፡፡በፌዴራል መንግስት የስልጣን እርከኖችም ተመጣጣኝ የስልጣን ዉክልናን ይዞ በሃገሪቱ የፖለቲካ ሂደት ዉስጥ ወሳኝ እና የማይተካ ታሪካዊ ሚናዉን በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡ ህዝቡ አስተዳዳሪዎቹን ከቀበል ጀምሮ እስከ ፌዴራል መንግስት በምረጫ ካርዱ እወሰነ ነዉ፡፡ የፈለገዉን ይመርጣል፡፡ ያልፈለገዉን በምርጫ ካርዱ ይቀጣል፡፡ በፈለገዉ ፖለቲካ ድርጅት ፣ የብዙሃን ና የሙያ ማህበራት ተደራጅቶ መብቱን እና ጥቅሙን ለማስከበር በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

ታዲያ «የፖለቲካ ጭቆናዉ» ከዬት መጣ? ደረቅ ወንጀል ፈጽመዉ በፍርድ ቤት ዉሳኔ ተሰጥቶባቸዉ በማረሚያ ቤት የሚገኙ ወገኖችን በመቁጠር ይህን ያሕል ሺነ የኦሮሞ ብሄር ተወላጆች «የፖለቲካና የሂሊና እስረኛ» ናቸዉ ብሎ አስመስሎ ማቅረብም ብሄራዊ ጭቆና አለ ለማለት አያስችልም፡፡ አሁንም አነጀዋር ሌላ አጀንዳ ካላመጡ በስተቀር ህዝቡ ጋር ወርደዉ «የፖለቲካ ጭቆና ስላለብህ በመገንጠል ነጻ ልናወጣህ መጣን» ቢሉት ያዉ እንደ ለመዱት (« badi asii») «ጥፉ ከዚህ!!» ይላቸዋል፡፡ አሁንም በዚያ ሜንጫ!! አላማቸዉ በጠባብ ብሄርተኝነት ነድተዉ ገንጥለዉ ለመጨቆን እንደሆነ ተገንዝቧል፡፡ ከምንም በላይ ግን ሕዝቡ ብሄራዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቱ ተከብሮለት የአዲሲቷ ኢትዮጲያ አንድነት የጀርባ አጥንት እንድሆነ ተቀብሏል፡፡

**2.2 «ኦሮሞፎቢያ» ወይስ የጀዋር የተሳሳቱ ሃሳቦች ፎቢያ**

በቃለ ምልልሱ ወቅት ጀዋር በተሳሳተ ድምዳሜ ትክክለኛ ያልሆነ ሃሳብ አራምዷል ብየ የማነሳዉ ነጥብ የሌሎች ብሄር ተወላጆች ኢትዮጲያዉያን የኦሮሞን ህዝብ እንደህዝብ የሚጠሉና የሚፈሩ «የኦሮሞ ፎቢያ» ያለባቸዉ ናቸዉ ብሎ በጅምላ መፈረጁ ነዉ፡፡ እንደኔ አስተሳሰብ ይህ ፍረጃ ግልብ የሆነ ግምገማ እና ከአንድ የፖለቲካ ሳይንስ ሀሁ ቆጥሬያለሁ ከሚል ግለሰብ የማይጠበቅ የተሳሳተ ድምዳሜ ነዉ፡፡ ጀዋር ከልክ ያላፈ ስሜታዊነት የሚያጠቃዉ ችኩል ሰዉ ነዉ፡፡ ከስሜታዊነቱ እና ከችኮላዉ ተነሳ ብዙ የተሳሳቱ እና አደገኛ አስተያየቶችን ይሰነዝራል፡፡ በሰነዘረዉ ሃሳብ የትችት ናዳ ይወርድበታል፡፡ ( «ኦሮሞ ፈርስት» ፣ «ኦሮሞ እንጂ ኢትዮጲያዊ አይደለሁም»፣ እና «በሜንጫ አንገቱን!» የሚሉትን አስተያየቹን ልብ ይሏል)፡፡ እዚህ ጋ ነዉ እንግዲህ ችግሩ፡፡ የተሳሳቱ የጀዋር አስተሳሰቦችን ነቅሰዉ አዉጥተዉ የነቀፉት ሁሉ የኦሮሞ ህዝብን እንደነቀፉ፤ ጀዋርን ሳይሆን የተሳሳቱ የጀዋር አስተሳሰቦችን የጠሉ ሁሉ የኦሮሞ ህዝብን የጠሉ አድርጎ ሌሎችን «ኦሮሞ ፎቢያ» አለባቸዉ ብሎ የደመደመዉ፡፡ በእኔ እምነት ጀዋር ስላቀረባቸዉ ሃሳቦች የተሰነዘሩት ትችቶች «ኦሮሞ ፎቢያዊ» ሳይሆኑ የተሳሳቱ የጀዋር አስተሳሳቦች ፎቢያዊ ናቸዉ ብየ አምናለሁ፡፡ ምክኒያቱም ጀዋር ሲቸኩል፣ ሲተነትንም ሆነ ሲሳሳት ራሱን እንጂ ህዝቡን ወክሎ አይደለም፡፡ ትችቶቹም ባቀረባቸዉ ሃሳቦች ላይ ያነጣጠሩ እንጂ ከህዝቡ ጋር ምንም የሚያገናኛቸዉ ነገር የለም፡፡ በግለሰብ ደረጃ የደረሰበትን ትችት በብሄር ዋሻ ዉስጥ በመከተት «እኔን የነቀፈ ብሄሬን ነቀፈ»፤ «የኔን ሀሳብ የጠላ ብሄሬን ጠላ» ስለዚህ «የኦሮሞ ፎቢያ አለበት» ብሎ መደምደም ስህተት ነዉ፡፡ ይህ ሰዉ እንቅፋት እንኳ ሲመታዉ «ኦሮሞ ስለሆንኩ ነዉ የመታኝ» የሚል አድሃሪ የሆነ አስተሳሰብ ማራመዱ አይቀርም የሚል ግምት አለኝ፡፡

የኦሮሞ ህዝብ እንደህዝብ የሚጠላበት እና በጥርጣሬ የሚታይበት «ፎቢያ» የሚሆንበት ምንም ዳራ የለዉም፡፡ ኦሮሞ ኩሩ እና ጀግና ኢትዮጲያዊ ነዉ፡፡ ኢትዮጲያን ለመዉረር የቃጡ ሃይሎችን የተፋለመ፣ ለሃገር ሉዓላዊነት ደም እና አጥንቱን የገበረ፣ዉድ ህይወቱን ለሃገሩ በመሰዋት በነፃነት ያቆየን ሕዝብ ነዉ፡፡ ከአድዋ እስከ ማይጨዉ፤ ከኦጋዴን እስከ ባድመ ኦሮሞ ልጆች ደም ከሌሎች ኢትዮጲዉያን ደም ጋር ተቀላቅሎ ፈሷል፡፡ አብረዉ ቆስለዋል፡፡ አብረዉ ደምተዋል፡፡ ባፈሰሱት ደምም ድልን ተቀዳጅተዋል፡፡ አብረዉ ተደስተዋል፡፡ ተጋብተዉ ተዋልደዋል፡፡ ይህን መሰለ አብሮነት ታሪካዊ ዳራ እለ ታዲያ በምን ስሌት ሌላዉ ኢትዮጲያዊ የኦሮሞ ፎቢያቲክ የሚሆነዉ?

የጀዋር «የኦሮሞፎቢያ» አስተሳብ ከጠባብ ብሄርተኝነት የሚመነጭ ሃሳባዊ «የአዕምሮ ግድግዳ» እንጂ ተጨባጭ እዉነታ አይደለም፡፡ እኔ እንደሚገባኝ ሌላዉ ኢትዮጲያዊ የኦሮሞ ፍቅር እንጂ ጥላቻ እና ፎቢያ የለዉም፡፡ በባልቻ አባ ነፍሶ፣ በአብዲሳ አጋ ፣ በአበበ ቢቂላ፤ በደራርቱ ቱሉ ወዘተ ጀግንነት የማይኮራ ኢትዮጲያዊ የለም፡፡ አነዚህ ጀግኖች ከልቡ የማይወድ ኢትጲዮያዊ የለም፡፡ እነዚህ ዉድ የኢትዮጲያ ልጆች ኦሮሞዎቸ ናቸዉ፡፡ እነዚህን ሰዎች የሚወድ በነሱ የሚኮራ ኦሮሞነታቸዉን ነጥሎ ሊጠላና ሊፈራ አይችልም፡፡

በመጨረሻም እነጀዋር «የኦሮሞ ህዝብ ሆይ ሌላዉ ኢትዮጲያዊ ይጠላሃል፡፡ ይጠራጠረሃል፡፡ የኦሮሞፎቢያ አለበት ከዚህ ጥላቻ ልናላቅቅህ ነዉ የምንታገለዉ፡፡ ለዚህም መፍትሄዉ መገንጠል ነዉና ተነስ!» ብለዉ አጀንዳ ይዘዉ ወደ ህዝቡ ቢወርዱ ሕዝቡ ምን ይላቸዉ ይሆን?